# ጥናት አንድ 1ኛ ጢሞ 1፡1-20

የጥናት ዓላማ፡- ትክክለኛን ትምህርት መማርና ራሳችንን በቃሉ እውቀት መሙላት እንደሚኖርብን ቢታወቅም፤ የጤናማ ትምህርት ዓላማና ግብ ግን፤ እውቀታችን የእግዚአብሄርን ፍቅር በውስጣችን የሚያቀጣጥል ነዳጅ ሊሆን ይገባዋል የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የዚህ ትዕዛዝ ዓላማ ግን ከንጹህ ልብ፣ ከበጎ ህሊና፣ እንዲሁም ከእውነተኛ እምነት የሚገኝ ፍቅር ነው፡፡›› 1ኛ ጢሞ 1፡5

1. 1ኛ ጢሞ 1፡1-20 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ስንመለከት ጸሐፊው ራሱንና መልዕክቱ የተጻፈለትን ሰው ምን በማለት ነው የሚያስተዋውቀው? ክፍሉ እግዚአብሄ አብንና ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በምን አይነት መጠሪያ ነው ሲጠራቸው የምንመለከተው?
2. ቁ3-7 ሳይ ስናነብ የጢሞቴዎስ ተልዕኮ ምን ነበረ? በሐዋ ሥራ 20፡29-31 ላይ ጳውሎስ የተናገረውን ሃሳብ በዚህ ክፍል ጢሞቲዎስ ከታዘዘው ነገር ጋራ በማነጻጸር ስንመለከተው አንድ ግልጽ ሆኖ የሚታየው ነገር ምንድነው?
3. በቁ6 ላይ ‹‹አንዳንዶች ከእነዚህ ነገሮች ዘወር ብለው…›› ብሎ ሲናገር ከየትኞቹ ነገሮች ማለቱ ነው? ሐዋርያው ከላይ ስለፍቅር ከተናገረው ነገር አንጻር ስንመለከተው፤ እነዚህ በቁ6-7 ላይ የህግ አስተማሪዎች በመባል የተጠቀሱት ሰዎች የሚያስተምሩት ትምህርት እንደ ከንቱ ንግግር የተቆጠረበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ትገምታለህ?
4. ቁ8 ‹‹ነገር ግን ሰው በአግባቡ ከተጠቀመበት ሕግ መልካም መሆኑን እናውቃለን፡፡›› ሕግን በአግባብ መጠቀም የሚለውን አነጋገር እንዴት ትረዳዋለህ? በቁ11 ላይ ጳውሎስ ጤነኛ ትምህርት በማለት የሚናገረው ስለየትኛው ትምህርት ነው? በራስህ ህይወት ሕግን ያለአግባቡ የተጠቀምክበት ጊዜ አለ ብለህ ታምናለህ ወይ?
5. ቁ12-14 ጳውሎስ ምን ዓይነት ሰው እንደነበረ፣ ጌታ ምን እንዳደረገለትና ለምን እንደተደረገለት ተናገር፡፡ የራስህን ህይወት በመመልከት ከእርሱ በምን እንደሚመሳሰል ወይም እንደሚለይ አስረዳ፡፡
6. በቁ15-17 ላይ ሐዋርያው ራሱን የሚያይበትን መንገድ ተናገር፡፡ በቁ15 ላይ የጌታን ተልዕኮ እውነተኛነት ለማረጋገጥ የተጠቀመበት ተጨባጭ ሁኔታ ምንድነው ትላለህ? ጳውሎ የተሰማው የምስጋና ስሜት በአንተስ ውስጥ ይፍለቀለቃል ወይ?
7. ቁ18-20 ስናነብ ጳውሎስ በእምነት ልጁ ለሆነው ለጢሞቴዎስ የሚሰጠው ትዕዛዝ ምን የሚል ነው? መልካምን ገድል ለመጋደል የሚያስፈልጉን በዚህ ክፍል የተጠቀሱ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ቁ20ንና 1ኛ ዮሐ 2፡27 ስናይ አማኝ የሚማርባቸው ስንት መንገዶች ታያለህ? እነዚህስ ምን ምንድናቸው?
8. ወደኂላ መለስ ብለን ቁ5ት ላይ ስንመለከት፤ ጳውሎስ ይህንን ትዕዛዝ የሰጠበትና ጢሞቲዎስ ደግሞ እነዚህን ሰዎች ከትክክለኛው ትምህርት ዘወር እንዳይሉ የሚያዝበት ዓላማ ሆኖ የተነገረው ነገር ምንድነው? የአንተስ ቃሉን ማጥናትህ በእግዚአብሄር ፍቅር እንድታድግ ረድቶሃል ወይስ የአዕምሮ ማዳበሪያ ብቻ ሆኖልሃል? ቃሉን ማጥናትና ማወቅህ አግዚአብሄርን ደስ ቢያሰኘውም እንኳን፤ እውቀትህ እርሱንና የእርሱ የሆኑትን አብልጠህ ወደማፍቀር የሚያመጣህ ሊሆን ይገባል፡፡

# ጥናት ሁለት 1ኛ ጢሞ 2፡1-15

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ስለሚፈልግ ከወሰዳቸው ከተለያዩ እርምጃዎች መሃል አንዱና ዋነኛው ለእኛ ለአማኞች የተሰጠው ታላቁ ተልዕኮ በመባል የሚታወቀው ሲሆን፤ እያንዳንዳችን ተልዕኮአችንን ለመወጣትና የልቡን መሻት ለመሙላት መትጋት እንደሚኖርብን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እርሱ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን ወደማወቅ እንዲደርሱ ይፈልጋል።›› 1ኛ ጢሞ 2፡4

1. 1 ጢሞ 2፡1-15 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በቅዱሳን ማህበር እንዲካሄድ ጢሞቲዎስን የሚያሳስበው ነገር ምንድነው? እነዚህ ነገሮች መደረግ የሚኖርባቸው እነማንን አስመልክቶ ነው?
2. ጳውሎስ በቤተ ክርስትያን ውስጥ ለሚካሄደው ጸሎት ትኩረት እንደሰጠው የምናውቀው በምንድነው? ‹‹አሳስባለሁ›› የሚለው አነጋገር ትዕዛዝን ወይስ ምንን የሚያመለክት ነው? በአገራችንም ሆነ በተለያዩ አገሮች ስለሚታዩት የአስተዳደራዊ ጉድለቶች ብዙ እንናገራለን፤ ‹‹ከሁሉ አስቀድሞ…›› የሚለውን የጳውሎስ አባባል አማኝ ሁሉ ቢከተል ምን ያህል ለውጥ ሊኖር ይችላል ብለህ እንደምታምን ከወገኖች ጋራ ተወያዩበት።
3. ቁ1-4ትን ስንመለከት ለሰዎች ሁሉ፣ ለነገሥታትና ለባለ ሥልጣናት ሁሉ መጸለይ አስፈላጊ ሆኖ ከሚገኝባቸው ምክንያቶች መሃል ሃዋርያው የጠቀሳቸውን ቢያንስ ሶስቱን ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። እነዚህን ነገሮች ስትመለከት ጸሎቱ ማካተት እንደሚኖርበት ግልጽ ሆኖ የሚታየን አንድ ነገር ምንድነው ትላለህ? ያንተስ ጸሎት የእግዚአብሄር የልብ ትርታ የሆነውን የሰዎችን ደህንነት ያካተተ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ?
4. ቁ5-6 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስን በምን ዓይነት ነው ሐዋርያው የሚያስተዋውቀው? ጌታ ኢየሱስ ለዚህ ዓይነቱ ሥፍራ መብቃቱን ያረጋገጠበት መንገድ ምንድነው? ቁ4 ላይ ‹‹ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ…›› ቁ6 ላይ ደግሞ ‹‹ራሱንም ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ›› የሚሉት አባባሎች ኢየሱስ ስለሞተላቸው ሰዎች ቁጥር ምን ይጠቁመናል?
5. ቁ7 ላይ ጳውሎስ የራሱን ማንነት ለመግለጥ የተጠቀመባቸው ሶስት ሃሳቦች ምን ምንድናቸው? እነዚህ ከጌታ የተቀበላቸው ሶስት ነገሮች በጳውሎስ ዓይን የሚታዩት በምን ዓይነት ነው? እግዚአብሄርን እንድታገለግለው ለአንተስ ከመንፈስ ቅዱስ የተቀበልከውን የጸጋ ሥጦታ የምታየው እንደ ሹመት ወይስ እንደ ሥራ?
6. ቁ8-10 ያለው ክፍል ወንዶችን አስመልክቶ የሰጠው ትዕዛዝ ምን የሚል ነው? በዚሁ ክፍል ውስጥ ስለሴቶች የተናገራቸው ነገሮችስ ምን ምንድናቸው? በዛሬው ጥናታችን በተለይም ከቁ9 ጀምሮ ስንመለከት ጳውሎስ የሰጠው ትዕዛዝ ሴቶችን ሁሉ የሚመለከት ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ።
7. ቁ11-15 ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቅዱሳንን በሃሳብ ከሚለያዩት ነገሮች አንዱ ነው። ጸሐፊው ለጢሞቲዎስ በተለይ በቁ11-12 ላይ ስለሴቶች የሚሰጠው መመሪያ ምን የሚል ነው? ለዚህስ ምክንያት አድርጎ የሚያቀርባቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? እያንዳንዱ የጥናት ተካፋይ በዚህ ጥቅስ ላይ ያለውን አመለካከት ለወገኖች ያካፍል፤ በአመለካከት መለያየት እንደሚኖርም አንዘንጋ። ፊሊ. 3፡15-16
8. ቁ4 ላይ መለስ ብለን ስንመለከት፤ አዳኛችን እግዚአብሄር ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና አውነትን ወደማወቅ እንዲደርሱ ከመፈለጉ የተነሳ፤ ሰዎችን ለማዳን የወሰዳቸውና እየወሰደ ያለው ምን ምን እርምጃዎች ይታይሃል? በዚህ በእግዚአብሄር ፕሮግራም ውስጥ የአንተ ተሳትፎ ምንድነው ብለህ ታምናለህ? እግዚአብሄር ሰዎችን ለማዳን ከሚጠቀምባቸው ነገሮች መሃል አንዱና ዋነኛው ለአማኞች የሰጠው ሂዱና ወንጌልን ለአለም ሁሉ ንገሩ የሚለው ስለሆነ ሃላፊነትህን ልትወጣ ያስፈልግሃል።

# ጥናት ሶስት 1ኛ ጢሞ 3፡1-16

የጥናት ዓላማ፡- እያንዳንዳችን በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ ስንመላለስ ለሁሉም ነገር ስርዓት እንዳለው ማወቃችን እጅግ አስፈላጊ ሲሆን፤ መሪዎችም ይህንን ተገንዝበው ህዝቡን የማስተማር ግዴታ እንዳለባቸው እንዲረዱ ለማድረግ።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ወደ አንተ ቶሎ ለመምጣት ተስፋ ባደርግም ይህንን ትእዛዝ እጽፍልሃለሁ፤ ይህንም የምጽፍልህ ብዘገይ እንኳ ሰዎች በእግዚአብሄር ቤት እንዴት መኖር እንዳለባቸው እንድታውቅ ነው።›› 1ኛ ጢሞ 3፡14-15

1. 1ኛ ጢሞ 3፡1-16 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ። በዛሬው ምንባብ መሰረት የቤተ ክርስትያን ሽማግሌ ወይም ኤጲስ ቆጶስ ለመሆን በቅድሚያ የሚያስፈልገው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? የቤተ ክርስትያን ሽማግሌ ለመሆን በቅድሚያ ያለውን ነገር ያሟላ ሰው ያ ብቃውን በቂ ሊሆነው እንደማይችል የምንረዳው እንዴት ነው?
2. በቁ2-3 ውስጥ ከኤጲስ ቆጶስ ስለሚጠበቁት ባህርያት ጳውሎስ የዘረዘራቸውን አንድ በአንድ ተናገር። ‹‹ማስተማር የሚችል›› የሚለውን መመሪያ እንዴት ትረዳዋለህ? ከዝርዝሮቹ ውስጥ ገንዘብን አለመውደድ እንደ አንድ ሆኖ የገባበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል? ቤተ ክርስትያን ይህንን የገንዘብ ወዳድነትን መመሪያ ትኩረት ሰጥታ በመመሪያነት ተጠቅማበታለች ብለህ ታምናለህ ወይ?
3. ቁ4-5 ያለውን ክፍል ስናነብ ቤተ ክርስትያንን በሽምግልና ለማስተዳደር እንደ ቅድመ ሁኔታ አድርጎ ጳውሎስ የሚናገረው ነገር ምንድነው? በቁ6-7 ላይ ሌሎች በተጨማሪነት የተሰጡት ሁለቱ መመሪያዎች ምንና ምንድናቸው? የቤተ ክርስትያን ሽማግሌ ለመምረጥ እድል ሲሰጥህ እነዚህን መመሪያዎች ተመርኩዘህ ለመምረጥ ሙከራ አድርገሃል ወይ?
4. በቁ6-7 ላይ የቤተ ክርስትያን መሪ ከመሆን ከተጠቀሱት ሁለቱም ነገሮች ጋራ የዲያቢሎስም ስም ተጠቅሶ እንመለከታለን። የዲያቢሎስ ወጥመድ ሆኖ በዚህ ሥፍራ የተነገረለት ነገር ምንድነው? ለምን ይመስልሃል ሐዋርያው በትዕቢት የመነፋትን ነገር ከአዲስ ክርስትያን ጋራ ማያያዝ የፈለገው?
5. በቁ8-10 እና በቁ12-13 ውስጥ ደግሞ ስለ ዲያቆናት የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች እናነባለን። የኤጲስ ቆጶስ ወይም የቤተ ክርስትያን ሽማግሌንና የዲያቆናትን መመዘኛዎች ስታወዳድር በሁለቱም ውስጥ ያገኘሃቸውን መመዘኛዎች ተናገር።
6. ቁ11 ላይ ‹‹እንዲሁ ሴቶችም›› የሚለው አነጋገር አንዳንዶች የዲያቆናትን ሚስቶች ነው የሚናገረው፤ ሌሎች ደግሞ ሴቶች ዲያቆናትን ነው ይላሉ። ከዚህ አንጻር አንተ ከየትኛው ሃሳብ ጋራ ትስማማለህ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ።
7. ቁ15-16ት ላይ ስለ እግዚአብሄር ቤት የሚናገራቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? በዚሁ በቁ16 ላይ እውነተኛን የመንፈሳዊ ህይወት ምሳሌ ሆኖ በተለያዩ መግለጫዎች የተነገረው ማን ነው?
8. ከሃዋርያው ጳውሎስ አነጋገር በተለይም ቁ14-15ትን ስናነብ 1ኛ ጢሞቴዎስን የጻፈበት ዓላማ ምንድነው? በቶሎ ወደ እርሱ እንደሚመጣ እያወቀ ምን ያስቸኩለዋል፣ ለምን ፊት ለፊት ሲያገኘው አይነግረውም? የሰዎች በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ ስርዓት ይዘው መመላለሳቸው በአንተስ ዘንድስ ትኩረት ይሰጠዋል ወይ? ቅዱሳን በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ ስርዓት እንዳለ ማወቃቸውና መማራቸው ችላ ሊባል የማይገባውና መሪዎች ትኩረት ሊሰጡት የሚገባ ነገር ነው።

# ጥናት አራት 1ኛ ጢሞ 4፡1-16

የጥናት ዓላማ፡- በውስጣችን የምናስገባውና የምናስተናግደው የትምህርት ዓይነት የመንፈሳዊ ህይወታችንን ጤናማነት ሁኔታ የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም በሽተኞች ወይም ጤነኞች የማድረግ ሃይል እንዳለው ልንረዳ ያስፈልገናል። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ለህይወትህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፤ በእነዚህም ጽና፤ ይህንን ብታደርግ፣ ራስህንና የሚሰሙህንም ታድናለህና።›› 1ኛ ጢሞ 4፡16

1. 1ኛ ጢሞ 4፡1-16 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-2 ላይ ‹‹መንፈስ በግልጥ ይናገራል›› በማለት ጸሐፊው ይነግረናል። ስለዚህ ሁኔታ በዚህ ቁጥር ውስጥ የተነገሩን ቢያንስ አራት ነገሮችን ማየት እንችላለን፤ እነዚህ ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። የዚህ ትምህርት ምንጭ አድርጎ ሐዋርያው የሚያቀርባቸው ሰዎች እነማን ናቸው?
2. ቁ3ትን ስናነብ እነዚህ ሰዎች ከሚያስተምሯቸው ዓይነት ትምህርቶች መሃል በዚህ ክፍል የተዘረዘሩት ሁለቱ ምንና ምን የሚሉ ናቸው? የነዚህ ዓይነቶችን ትምህርቶች ጳውሎስ በቁ1 ላይ ሲናገር ከምን ጋራ ነው ሲያዛምዳቸው የምንመለከተው?
3. ጳውሎስ ስለ ምግብ አይነቶችና የትኛው እንደሚበላ የትኛው እንደማይበላ በቁ4-5 ውስጥ ከተናገረው ንግግር የማይበሉ ነገሮች ምን ምንድናቸው? ለምንድነው አማኞች ምግብን ሁሉ ለመብላት ድፍረትና ምክንያት አላቸው ማለት የምንችለው?
4. ቁ6-7ትን ስናነብ ‹‹ይህንን ትዕዛዝ...›› ሲል የሚናገረው ስለየትኛው ትእዛዝ ነው? ከዚህ ከቁ6 የምንመለከተው ጢሞቲዎስ ስለዚህ ሊመጣ ስላለው ነገር እንዲያውቅ ብቻ ሳይሆን፣ በተጨማሪ ምን እንዲያደርግ ነው የሚጠበቅበት? ጢሞቲዎስ በተለይም በቁ7 ላይ ምን ዓይነት ስልጠና ውስጥ እንዲገባ ነው የሚጠየቀው? ለዚህ ዓይነቱ ስልጠና የማይሆኑና ለእድገት እንቅፋት እንደሚሆኑ የተነገሩት ነገሮች ምንድናቸው?
5. በቁ8 ላይ ለእውነተኛ መንፈሳዊ ህይወት የሚደረገውን ስልጠና ጳውሎስ ከምን ጋራ ሲያነጻጽረው ነው የምንመለከተው? እነዚህ ሁለት ነገሮች ሲነጻጸሩ የትኛው ልቆ ነው የሚገኘው? አንተስ ለነፍስህ ወይም እግዚአብሄርን ለመምሰል ራስህን ታስለምዳለህ ወይ?
6. ጳውሎስና ጓደኞቹ ይህንን በቁ7-8 ያለውን ነገር ለሰዎች የሚሰብኩት ስብከት ብቻ እንዳልሆነና የእነርሱንም ህይወት የሚመለከት ነገር እንደሆነ ከቁ9-10 ማየት የምንችለው እንዴት ነው? ከቁ10 አነጋገሩ ስንመለከት ይህ እግዚአብሄርን ለመምሰል ራስን የማስለመድ ነገር ቀላል ሆኖ ታየዋለህ ወይ? ለምን?
7. ቁ11-14ትን ስናነብ የጢሞቲዎስን ወጣትነት ሰዎች እንዳይንቁት ካስፈለገ፤ እርሱ ማድረግ የሚጠበቅበን ነገር ምንድነው? ጢሞቲዎስ በህይወቱ ከሚያሳያቸው መልካም ኑሮ አልፎ ጳውሎስ በቅዱሳኑ ዘንድ እንዲያደርግ የሚጠብቅበት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
8. ቁ15-16ን ስናነብ በተለይ ቁ16 ላይ ጢሞቲዎስ ጥንቃቄ እንዲያደርግ የታዘዘው ሁለት ነገሮችና፤ እነዚህን ታዞ ቢያደርግ ስለሚያገኘው ውጤት ምን እናያለን? አንተስ ውስጥህ የምታስገባው ትምህርትና የመንፈሳዊ ህይወትህ ጤንነት እንደማይለያይ ገብቶሃል ወይ? በውስጣችን የገባው ትምህርት መንፈሳዊ ህይወታችንን ጤናማነት ሁኔታ ይወስነዋል።

# ጥናት አምስት 1ኛ ጢሞ 5፡1-25

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ቤተሰብ መሆናችን በቃል የምንናገረው እውነት ብቻ ሆኖ እንዳይቀርና፤ ዓለም ከውጭ ሆኖ ቤተ ክርስትያንን ሲመለከት እውነትም የቤተሰብ ዓይነት ፍቅርን መለማመዳችንን እንዲመሰክር ይገባል፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹አረጋውን ሰው እንደ አባትህ…ወጣት ወንዶችን እንደ ወንድሞችህ…አሮጊቶችን እንደ እናቶች… ወጣት ሴቶችን ደግሞ እንደ እህቶች በፍጹም ንጽህና አስተናግዳቸው፡፡›› 1ኛ ጢሞ 5፡1-2

1. 1ኛ ጢሞ 5፡1-25 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-2ትን በማንበብ አባት፣ እናት፣ ወንድምና፣ እህት የሚሉትን አነጋገሮች ስትመለከት፤ ጢሞቲዎስ ስለሚመራውና ስለሚያስተዳድረው ህዝብ ሊኖረው ስለሚገባው አመለካከት ምን ትረዳለህ? የእነዚህ የተለያዩ አይነት ሰዎች በቤተክርስትያኒቱ መገኘት ሌላ ምን ሊጠቁመን የሚችለው እውነት አለ ትላለህ?
2. ቁ3-6 ስናነብ ይህ ክፍል አማኝ እምነቱን በስራ መተርጎም የሚችለው በምን መንገድ ነው ይለናል? ቤተ ክርስትያን ምን ዓይነት መበለቶችን የመደገፍ ሃላፊነት ነው የሚኖርባት? ኪዚህ ክፍል አነጋገር እንደምትረዳው የእግዚአብሄርን ልብ ደስ የሚያሰኘው ነገር ምንድነው? እንደዚህ አይነቱን እግዚአብሄርን ደስ የሚያሰኘውን ቤተ ሰብን የመርዳት ነገር ምን ያህል ትለማመደዋለህ?
3. ቁ7-8ትን ስናነብ ጳውሎስ ይህንን ቤተሰብን የመርዳትና የመደገፍ ነገር በምን ዓይነት እንዲያቀርበው ነው ለጢሞቲዎስ የሚነግረው? ከቁ8 እንደምንረዳው ለዘመዶቹ ወይም ደግሞ ለቅርብ ቤተሰቡ የማያስብና እርዳታ የማያደርግን ሰው መጽሐፍ ቅዱሳችን በምን ዓይነት ነው የሚገልጸው?
4. ቁ9-11 ላይ ቤተ ክርስትያን ልትቀበልና ልትረዳ ስለሚገባት መበለቶች የተሰጡት መመሪያዎች ምን ምንድናቸው? ቁ9‹‹…በመዝገብ ላይ አትጻፍ›› ቁ11 ‹‹…መዝገብ አትጻፉቸው›› የሚሉትን አነጋገሮች ስታነብ በአንተ አመለካከት ስለ ቤተ ክርስትያን አሰራር ምን መማር እንችላለን ትላለህ?
5. 11-15 ላይ ጳውሎስ ወጣቶችን መበለቶች ቤተ ክርስትያን ተቀብላ እንዳትረዳ መመሪያ ይሰጣል፡፡ በዚህ ክፍል ቤተ ክርስትያን ወጣቶችን መበለቶች እንዳትቀበል የሰጣቸው ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ እነዚህን ወጣቶች መበለቶች ቤተ ክርስትያን ተቀብላ ከማስተናገድ ይልቅ ሐዋርያው እንዲደረግ የሰጠው ምክር ምን እንዲደረግ ነው?
6. ቁ17-18 ስለምን አይነት ሽማግሌዎች ነው የሚነግረን? በዚሁ ቁ17 ላይ ‹‹በሚገባ›› እና ‹‹የሚተጉ›› የሚሉት ሁለቱ ቃላት ስለ ሽማግሌዎች ሥራ የሚጠቁሙን ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? ‹‹እጥፍ ክብር ይገባቸዋል›› የሚለውን አነጋገር በቁ8 ካለው ሃሳብ ጋራ በማገናዘብ ስታነበው ምን ማለቱ እንደሆነ ነው የምትረዳው?
7. ቁ19-20ን ስንመለከት የቤተ ክርስትያን ሽማግሌን መክሰስ አስመልክቶ የተሰጡት ትዕዛዞች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ለምንድነው ሽማግሌ ሲገሰጽ በጉባኤ ፊት መሆን ያለበት?
8. ቁ21-25 ላይ በተለይም ቁ21ድን ስናነብ ሐዋርያው ጳውሎስ በጢሞቲዎስ አገልግሎት ውስጥ እንዳይከሰት እየሰጋ ያለው ነገር ምን ይመስልሃል? ይህንን እንዳያደርግ ሲነግረው የማስጠንቀቂያውን ጥብቅነት መረዳት የሚያስችለን ከአጻጻፉ ወይም ከአነጋገሩ ምን ነገር ታያለህ?
9. ቁ1-2 እንደምናየው ለእግዚአብሄር አገልጋይ ሰዎችን እንደ አባት፣ እንደ እናት፣ እንደ ወንድምና እንደ እህት ማስተናገዱ በጉባኤው ምን ዓይነት መንፈስ የሚፈጥር ይመስልሃል? አንተስ የእግዚአብሄርን ቤተሰብ እንደ እውነተኛ አባትህ፣ እናትህ፣ ወንድምና እህት አድርገህ ታያለህ ወይ? አንዳችን ሌላችንን የምንመለከትበት መንገድ በቃል ብቻ ሳይሆን አንዳችን ለሌላችን ከስጋ ባላነሰ መንገድ እንደ አባት፣ እናት፣ ወንድምና እህት ልንተያይ ይገባናል፡፡

# ጥናት ስድስት 1ኛ ጢሞ 6፡1-10

የጥናት ዓላማ፡- ባለጠጋ የመሆን ፍላጎት አዕምሯችንን ከያዘውና የእግዚአብሄርን ማንነት ለማወቅ ከምናደርገው ጥረት ይልቅ የገንዘብ ፍቅር ልባችንን ከያዘው፤ በመጨረሻ ወጥመድ ሆኖ ከእምነት ጎዳና ሊያወጣን እንደሚችል ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ነገር ግን እውነተኛ መንፈሳዊነት ባለን ነገር ከመርካት ጋራ ትልቅ ትርፍ ነው…ባለጠጋ ለመሆን ካላቸው ጉጉት የተነሳ ከእምነት መንገድ ስተው ሄደዋል፤ ራሳቸውንም በብዙ ሥቃይ ወግተዋል፡፡›› 1ኛ ጢሞ 6፡6-10

1. 1ኛ ጢሞ 6፡1-10 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ ጳውሎስ ምክር የሚሰጠው ለማን ነው? ጌቶቻቸው ሙሉ ክብረ እንደሚገባቸው እንዲቆጥሩ የታዘዙበት ምክንያት ለምንድነው? ከተሰጠው ምክንያት ጋራ ትዕዛዙን ስናገናዝብ፤ ይህ ትዕዛዝ ለማናቸውም ባሪያ ሁሉ የተሰጠ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን?
2. ቁ1ላይ የምናያቸውና በቁ2 ላይ የምናያቸው ጌቶች ልዩነታቸው ምንድነው? ብዙ ጊዜ በአማኞች ዘንድ የሚከሰትና ጳውሎስ በቁ2 ላይ ሊያስተካክል የሚሞክረው አንድ ችግር ምንድነው? ይህንን እርማቱን ምን በማለት ነው የሚያቀርብላቸው? እነዚህ ነገሮች በምክር በመናገር ብቻ የሚያልፋቸው ነገሮች እንዳልሆኑ የምንረዳበት መንገድ ምንድነው? አለቃህ አማኝና እግዚአብሄርን የሚፈራ በመሆኑ በሥራህ ከመትጋት የለገምክበት ጊዜ አለ ወይ?
3. በቁ3 ላይ የሐሰት ትምህርት በመባል የተነገረለት ነገር የሚጎሉትን ሁለት አበይት የሆኑ ነገሮችን በዚሁ ቁጥር ውስጥ ጠቅሷቸዋል፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? እንደዚህ ዓይነቶችን የሃሰት ትምህርቶች ስለሚያስተምር ሰው ቁ4 የሚናገራቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
4. እነዚህ የሃሰት አስተማሪዎች የሚዘሩት የክፉ ዘር በቁ5 መሰረት ፍሬ የሚያፈራው በምን ዓይነት ሰዎች ውስጥ ነው? ‹‹መንፈሳዊው ነገር ትርፍ ማግኛ በሚመስላቸውና…›› ከሚለው የጳውሎስ አነጋገር ስለ እዚህ ሰዎች አስተሳሰብ ምን ትረዳለህ? አንተስ እንደዚህ አይነት ሰዎች ገጥመውህ ያውቃሉ ወይ?
5. በቁ5-6 ላይ ማትረፊያ የሚመስላቸው ሰዎች እንዳሉ ሁሉ ማተረፊያ የሚሆንላቸው ሰዎችም እንዳሉ እንመለከታለን፡፡ እነዚህ ሁለቱ ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው? ለምን ይመስልሃል ‹‹ከመርካት ጋራ›› በማለት በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄርን መምሰልን ከእርካታ ጋራ ማቆራኘት ያስፈለገው?
6. ቁ7-8 ላይ ማናቸውም ሰው በልቡ ጽላት ላይ ቢጽፈው የሚጠቅም ጳውሎስ የተናገረው ምን እውነት ይታይሃል? ይህ እውነት ለምንድነው ሰው በተግባር ቢያውለው ነጻ የሚያወጣ ሊሆን የሚችለው? በዚህ ምድር ላይ ስንኖር የግድ ያስፈልጉናል ብሎ ጳውሎስ የሚናገራቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? አንተስ እነዚህ ሁለት ነገሮችን እግዚአብሄር አጉሎብህ ያውቃል ወይ?
7. ቁ9 ላይ ባለጠጋ ለመሆን የሚፈልጉ ሰዎችን መጨረሻ አስመልክቶ ምን እንደሚናገር አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር፡፡ በአንደኛነት የተጠቀሰው ነገር ወደ ፈተና እንደሚወድቁ ነው፤ ምን ይመስልሃል ለእነዚህ ሰዎች ፈተና የሚሆንባቸው ነገር? ‹‹ወጥመድ›› የሚለውስ ሃሳብ ከዚህ ሃብታም መሆን ከመፈለጋቸው ጋራ ሊኖረው የሚችለው ግንኙነት ምንድነው? ባለጠጋ የመሆን ፍላጎት ምን ያህል ህይወትህን ይቆጣጠረዋል?
8. በቁ10 ላይ የምናያቸው ሰዎች ከእምነት መንገድ ስለሳቱበት ምክንያት ምን ይነግረናል? በቁ6 ላይ ባሉት ሰዎችና በቁ10 ላይ ባሉት ሰዎች መካከል የምናየው ልዩነት ምንድነው? እግዚአብሄር በባረከህ ነገር የመርካትና የእርሱን ፊት በመፈለግ ላይ ትበረታለህ ወይ? ባለጠጋ የመሆን ፍላጎት አዕምሮህን ከያዘውና የእግዚአብሄርን ማንነት ለማወቅ ከምታደርገው ጥረት ይልቅ ሃብት ማካበት የመጀመሪያ ቅድሚያ ካደረከው በመጨረሻ ወጥመድ እንደሚሆንብህ አትዘንጋ፡፡

# ጥናት ሰባት 1ኛ ጢሞ 6፡11-21

የጥናት ዓላማ፡- እኛ የተጠራነው ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት እንድናድግና እርሱን ለመምሰል የጽድቅን መንገድ እንድንከተል እንጂ ባለጠጋ ለመሆን ስላልሆነ፤ ጌታ በማቴ 6፡33 ውስጥ እንዳሳሰበን ገንዘብም ሆነ ሌሎች ማናቸውም ነገሮች የሚከተሉ በረከቶች ሊሆኑ እንደሚገባ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ባለጠጋ ለመሆን የሚፈልጉ ግን ወደ ፈተናና ወደ ወጥመድ እንዲሁም ሰዎችን ወደ መፍረስና ወደ ጥፋት ወደሚያዘቅጠው ወደ ብዙ ከንቱና ክፉ ምኞት ይወድቃሉ፡፡›› 1ኛ ጢሞ 6፡9

1. 1ኛ ጢሞ 6፡11-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ11ድን ጸሐፊው ሲጀምር ‹‹የእግዚአብሄር ሰው ሆይ፤ አንተ ግን…›› በማለት የጀመረው ጢሞቲዎስን ከማን ጋራ በማነጻጸር ነው? በቁ11 ላይ ስለ ሽሽትና ስለ መከታተል ይናገራል፤ ጢሞቲዎስ እንዲሸሽ የተነገረውና እንዲከታተል ደግሞ የተመከረው ምን ምን ነገሮች ነው? ይህ ትዕዛዝ ለጢሞቲዎስ ብቻ ሳይሆን እኛን ሁሉ የሚመለከት መሆኑን የሚጠቁምህ የትኛው አነጋገር ነው?
2. በቁ12 ላይ ጳውሎስ ጢሞቲዎስን የሚያበረታታው ምን እንዲያደርግ ነው? በ2ኛ ጢሞ 4፡7 ላይ ስለራሱ በተናገረው አነጋገርና በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ ለወጣቱ አገልጋይ በተናገረው ነገር መሃል የምትመለከተው ተመሳሳይነት ምንድነው? ለምን ይመስልሃል ሃዋርያው ይህንን ገድል ወይም ጦርነት መልካም በማለት የሚናገርለት? የገባህበት የክርስትና ህይወት ተጋድሎ ያለበት እንደሆነ ገብቶሃል ወይ?
3. በቁ13-14 ውስጥ ሐዋርያው እግዚአብሄርን በምን ዓይነት ስያሜ ነው የሚጠራው? ጢሞቲዎስ ጳውሎስ የሚሰጠውን ዓደራ እንዲታዘዝ የሚጠበቅበት እስከመቼ ድረስ ነው? ለምንድነው አደራው እስከዚህ እስከተጠቀሰው ቀን ብቻ እንዲጠብቅ የተነገረው?
4. በቁ15-16 ላይ ለእግዚአብሄር የተሰጡ መጠሪያዎች የምትላቸውን ሁሉ አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመገለጫ ቀን እነኚህ ቁጥሮች ምን ያረጋግጡልናል?
5. በቁ9 እና በቁ17 ላይ በተጠቀሱት ሰዎች መካከል ምን ልዩነት ታያለህ? በቁ17 ላይ ጳውሎስ ከሚናገረው አነጋገር በመነሳት፤ በዚህ ዓለም ሃብት ባለጠጋ መሆን ሊያስከትል የሚችለው ምን አደጋ ትመለከታለህ? ከጳውሎስ አነጋገር እንደምንረዳው በዚህ ክፍል ባለጠጎች የተባሉት ገንዘቡን እንዴት ነው ያገኙት?
6. ጳውሎስ በቁ18 ላይ ለባለጠጎች እንዲደርሳቸው የሚፈልገው መልዕክት ምን የሚል ነው? በቁ17 ላይ ‹‹ደስም እንዲለን ሁሉን ነገር አትረፍርፎ በሚሰጠን…›› የሚለውን አነጋገርና በቁ18 ላይ ደግሞ ‹‹ለማካፈል ፈቃደኞች የሆኑ›› ከሚሉት አነጋገሮች ልንማር የምንችለው እውነት ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ ባለህ ነገር መልካም ማድረግና ማካፈል ምን ያህል ትለማመዳለህ?
7. በገንዘባችን መልካምን ነገር መሥራትና ለሌሎች ካለን በማካፈል የሚያስገኘው በረከት ምንድነው?
8. በቁ20 እና 21 ላይ ጢሞቲዎስ እንዲርቅ የሚነገረው ከምንና ከምን ዓይነት ነገሮች ነው? በዚህ ክፍል ‹‹እውቀት›› እያለ ጳውሎስ የሚናገረው ስለምን ዓይነት እውቀት ነው? የዚህ ዓይነቱን እውቀት የተከተሉና በዚያ ጎዳና ስለተመላለሱ ሰዎች መጨረሻ የተነገረን ነገር ምንድነው?
9. የዛሬውን ጥናት በአጠቃላይ ስንመለከት ጳውሎስ አማኞች ባለጠጋ መሆናቸውን ይቃወማል ብለህ ታምናለህ ወይ? ካልሆነስ የሚቃወመው ምን ዓይነትን ሃሳብና አመለካከት ነው? ባለጠጋ የመሆን መሻትህ እግዚአብሄርን ለመሻት ያለህን ፍላጎት አሸንፎብሃል ወይ? የምንከተለው ገንዘብን ሳይሆን፤ ጽድቅን፣ ፍቅርን፣ ትዕግስትን፣ ገርነትንና የመሳተሉትን ሆኖ ገንዘብ ግን በማቴ 6፡33 አይነት እኛን የሚከተለን ሊሆን ይገባል፡፡